የሰበር መ/ቁ. 24269

ኀዳር 24 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር ታረቀኝ ሞላ ቀረበ፡፡

ተጠሪ፡- ተክለማርያም መኮንን ቀረበ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለአቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ ተጠሪ ባቀረበው የቤት ይለቀቅልኝ ጥያቄ ላይ የተመሠረተ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀረመበት የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ተጠሪ የከሰሰው አዳነ ገብሩ እና ወ/ሮ ፈትለወርቅ ጌታቸው የተባሉትን ሰዎች ሲሆን፣ አመልካች ክርክሩ ውስጥ የገባው ለክርክሩ መነሻ በሆነው ቤት ላይ የተነሣው ጥያቄ ይመለከተዋል ስለተባለ ጣልቃ እንዲገባ ታዞ ነው፡፡ ተጠሪው ክስ የመሠረተውም በወረዳ 17 ቀበሌ 15 ክልል የሚገኝ ቁጥር 367/ለ/ የሆነው ቤት የግል ንብረቴ ሲሆን አዳነ ገብሩ በተባለው ተከሣሽ በውል አከራይቼው ሲጠቀምበት ቆይቶአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ከኔ ፈቃድ ውጪ ለወ/ሮ ፈትለወርቅ ጌታቸው አከራይቶታል፡፡ ስለዚህ ተከሣሾች ኪራዩን እንዲከፍሉና ቤቱን እንዲያስረክቡኝ ሊወስንልኝ ይገባል በማለት ነው፡፡ ፍ/ቤቱም ከተከሣሾች እና ከጣልቃ ገቡ የቀረቡትን የመከራከሪያ ነጥቦች ከሰማ በኂላ፣ 1ኛ ተከሣሽ እና ጣልቃ ገቡ ቤቱን ለከሣሽ ያስረክቡ፣ ከመስከረም ወር 1993 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ሰኔ 30 ቀን 1994 ዓ.ም. ድረስ ያለውን የኪራይ ገንዘብም በአንድነትና በነጠላ ይክፈሉ ሲል ወስኖአል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ ከአሁኑ አመልካች ይግባኝ የቀረበለት የፌ/ከ/ፍ/ቤትም ውሣኔው ጉድለት



የለበትም በማለት ይግባኙን ሳይቀበለው ቀርቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡

የሰበር ችሎቱ አመልካች ሚያዝያ 4 ቀን 1998 ዓ.ም. በፃፈው ማመልከቻ የቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርቦ ክርክሩን ሰምቶአል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው ተጠሪ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤት የሠራው ባልተፈቀደለት የከተማ ቦታ ላይ ነው እየተባለ ቤቱን ሊረከብ ይገባል የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም በጭብጥነት የተያዘው ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከሥር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር ይዘት መገንዘብ እንደቻልነው ተጠሪ ቤቱን ሠርቻለሁ በሚል ለሌላ ሰው በውል አከራይቶ ከመገኘቱ በቀር በቦታው ላይ ቤት እንዲሠራ አግባብ ካለው ባለስልጣን የተፈቀደለት ወይም በቦታው የመጠቀም መብት ያገኘ መሆኑን ለማስረዳት ያቀረበው ማስረጃ የለም፡፡ የሥር ፍ/ቤቶችም አቤቱታ የቀረበበትን ውሣኔ የሰጡት ማስረጃ አግኝተናል በማለት ሳይሆን፣ አመልካች ቤቱ ያረፈበት የከተማ ቦታ ለመወረሱ /የመንግሥት ንብረት ለመሆኑ/ ማስረጃ አላቀረበም የሚል ምክንያት በመስጠት እና ቤቱ በሕገ ወጥ መንገድ የተሠራ ነው ከተባለም የሚመለከተውና ሥልጣን ያለው አካል ነው ተገቢውን እርምጃ የሚወስደው የሚል ትችት በማከል ብቻ ነው፡፡

ለሁሉም ግልጽ እንደሆነው የከተማ ቦታና ትርፍ ቤትን የመንግሥት ንብረት ለማድረግ የወጣው አዋጅ ቁ. 47/67 ከታወጀ ወዲህ የከተማ ቦታ የመንግሥት ሃብት ሆኖአል፡፡ ይህ ማለት በግል የሚያዝ የከተማ ቦታ የለም ማለት ነው፡፡ ግለሰቦች በከተማ ቦታ የመጠቀም /የመያዝ/ መብት የሚኖራቸው አግባብ ባለው የመንግሥት አካል /ባለስልጣን/ ሲሰጣቸው ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ የምናየው ግን ተጠሪ በቦታው ላይ ይጠቀም ዘንድ /ቤቱን እንዲሠራ/ ሳይፈቀድለት ነው ቤት ሠርቼ አከራየሁ የሚል ክርክር ያቀረበው፡፡ የከተማ ቤት አሠራርና አጠቃቀምን በተመለከተ በወጣው አዋጅ ቁ. 292/78 በአንቀጽ 7/1/ እንደተደነገገው ከሚመለከተው ባለስልጣን ፈቃድ ሳይኖር የተሠራ የከተማ